# እንኳን ደስ ያየለን ወንድማችን አቶ ማሙሸት አማረ እና ሌሎቹም ታጋዮች ስለተፈቱ ።

February 15, 2018

በተለይ ለወይዘሮ የሀረር ወርቅ የኢትዮጲያ ወርቅ እንዲሁም ለኢትዮፓትርዮት አዘጋጆች በሙሉ የኢትዮጲያ ህዝብ የማይረሳችሁ ሀቀኛ በቆራጥነት የምትታገሉ በመሆናቹ እንኳንም አብሮ ደስ ያለን አሁንም መላው ሀገራችን ያለ ቅድመ ሁኔታ እስከምትፈታ ቆራጡ ትግላችን ይቀጥላል።

ወይዘሮ የሀረርወርቅ ግን ለየት የሚያደርጋት አንደኛ ፡ ሁሉንም የፓለቲካ ድርጅቶች ያካተተ ስብሰባ አሜሪካን እንድታዘጋጅ ከጠየቀችው በማጣመር ጎን ለጎን ያቀረበችው ለአሜሪካን ይሄውም በኢትዮጵያ የሚገኘው ለዲሞክራሲ እና ለፍትህ ሲታገል በቲፒኤሌፍ ተይዞ የእስር ቤት እና የስቃይ እራት የሆነውን ኢትዮጵያዊ አንድም እስረኛ ሳይቀር ወንዱንም ሴቱንም ፡ አሜሪካን በብሄራቸው ሳይሆን በኢትዮጵያዊነታቸው ላይ ብቻ በማተኮር ሁሉንም እስረኞች ባስቸኳይ ከወያኔ እስር ቤት እንድታስፈታቸው ያደረገችው ሚስጥራዊ ስብሰባ በዋሽንግተን ዲሲ ልዩ ዘመቻ ሁለት ዘመቻ ይዛ በመመላለስ በተግባር እንዲውል ያደረገችው የእስረኞች መፈታት ነው።

ይሄንን ሁሉ ጎዞ በገዛ ገንዘብዋ ዲሲ በመመላለስ ያደረገችው መሆኑ አንዱ ልዩ የሚያደርጋት ተግባር ነው ከአብዛኛዎቻችን ። የሀረር ወርቅ የሰራቸው በተግባር እየዋለ መምጣቱን ያዩት እና ሁለቱም ጥያቄዎችዋ እና ዘመቻዋ ግቡን እንደሚመታ በሚገባ የተረዱት አሜሪካኖች ጉዳዩ የአለም አቀፍ ጋዜጠኞች ትልቅ ሽፋን እንዲሰጡበት አድርገዋል። ለዚህም የአሜሪካንን ድምጽ ቴሌቪዢን ኢንግሊሽ ቱን አፍሪካን እና ሬድዮን ጭምር (ስትሬት ቶክ አፍሪካ እና አፍሪካ 54 በሚል የሚታወቀው የሰጣትን ሽፋን መመልከቱ ትልቅ መረጃ ነው። ወጣቱ ታጋይ ማሙሸት አማረን ከእስር ቤት ለማስለቀቅ ምንም ጥረት የሚያደርግለት ባልተገኘለት ሰአት ብቸኛዋ ማሙሸትን  እንዲፈታ እና መኢአድን እንዲረከብ የታገለችለት የሀረር ወርቅ ናት። ወገኖችዋን ኢትዮጵያውያን ጀግኖችን ለማስፈታት የተለያዩ ጥረቶችን አድርጋ በመጨረሻም በልዩ መንገድ በመሄድ ተሳካለት።

አሁንም ስላልተለቀቁት እስረኞች  እየጣረች ነው። እግዚአብሄር እድሜዋን ያርዝምልን። በተጨማሪም መኢአድ ቦታ እንዲኖረው በአሜሪካን መንግስት በኩል አድርጋለች ስሙን አድሳለች። እንዲሁም ለአቶ ማሙሸት አማረ ፔትሽን አዘጋጅታ ሁሉንም ኢትዮጲያዊ እንዲፈርም በተለያዩ ዌብሳይት ላይ በፌስቡክ ጭምር በማውጣት ሁላችንም እንድንፈርምለት አድርጋለች ። ይህ ከብዙ በጥቂቱ ሲሆን ፡ ሌላው ወራዳ ዶክተር እና ግብረአበሮቹ ደግሞ ዶክተር በዛብህን የመኢአድ ሊቀመንበር ነው ብለው የወጣቱን የማሙሸት አማረን ኅይወት ከምንም ባለመቁጠር ከስር ቤት መቼም አይወጣም ብለው በመወሰን ፡ ዶክተር በዛብህን አስመጥተው ገንዘብ  ሲሰሩ ታይተዋል ። ከዲሲ ጀምሮ በየከተማው ዳላስ ጭምር ይዘውትም ዞረዋል።

መኢአድ ደካማ እና እራሱን ችሎ መቆም የማይችል አድርጎ ለማሳየትም ዶክተር በዛብህን ያመጣው ዶክተር እና ግብረአበሮቹ ብዙ ሞክረዋል። አሁን ማሙሸት ተፈቷል መኢአድ መሪ አለው በፊት አሁንም። ለማንኛውም ጀግናውን ማሙሸት አማረን ለማስፈታት የተባበራችሁ ደግ ያሰባች ሁሉ እንኳን ደስ ያላችሁ ትግሉ ይቀጥላል እንበርታ። አስመሳዮችን አሁን ማሙሸትን እየደወሉ ለሱ መፈታት የታገሉ

በማስመሰል እየተሯሯጡ ያሉቱን ቀዝቀዝ በሉ ሃሰት ታጠፋችኋለች እላለሁ።
ልብ ላጣውም ልብ ይስጥልን።

እዝራ